# የተማሪ CoAlt ELA እና የሂሳብ ነጥብ ሪፖርቶችን ማየት ለመቻል

## ጁን ወር ውስጥ በካይት (Kite) ቤተሰብ ፖርታል በኩል ይገኛል

የቅድሚያ CoAlt እንግሊዘኛ ቋንቋ ጥበባት (ELA) እና የሂሳብ የተማሪ አፈጻጸም ሪፖርቶች በጁን **13፣ 2025** በካይት (Kite) ቤተሰብ ፖርታል ውስጥ በኦንላይን እንደሚገኙ ስናካፍል ደስታ ይሰማናል። CoAlt ተማሪዎች የኮሎራዶ የአካዳሚክ መመዘኛዎችን የተራዘመ አስረጅ ውጤቶች (EEOs) የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማወቅ በስቴቱ በሞላ ላሉ ተማሪዎች የሚሰጥ ምዘና ነው። ይህ ደህንነቱ የተጠበቀ መድ ረክ (ፕላትፎርም) ስለ ተማሪዎ አፈጻጸም በELA እና በሒሳብ በ CoAlt ምዘና ላይ መረጃዎችን ለማየት ቀላል መንገድ ይሰጥዎታል።

የልጅዎን ሪፖርቶች ለማየት በየአመቱ በተማሪዎ የመመዝገቢያ ኮድ እና መታወቂያ ቁጥር መመዝገብ ይኖርብዎታል። ኢሜልዎን ካስመዘገቡ በኋላ፣ ለመግባት እና ሪፖርቶቹን ለማየት ለ24 ሰዓታት የሚሰራ ጊዜያዊ የመዳረሻ ኮድ ይደርስዎታል።

ለ 2024-2025 የትምህርት ዘመን ዳታ፣ በCoAlt DLM ELA እና በሒሳብ ምዘናዎች ላይ ለተሳተፉ ተማሪዎች CDE ሁሉንም የምዝገባ ኮዶች አውጥቷል/አዘጋጅቷል። እነዚያ በልጅዎ ትምህርት ቤት ለእርስዎ ይላካሉ።

## የልጅዎን CMAS/CoAlt ሪፖርት ማግኛ እርምጃዎች

- የ **Kite የቤተሰብ ፖርታል** https://parentportal.kiteaai.org/login ን ይጎብኙ
- ለመግባት የሚከተሉት መረጃዎች ያስፈልግዎታል፦
    - የተማሪ የስቴት መታወቂያ (SASID) - የልጅዎን የስቴት መታወቂያ በDPS የወላጅ ፖርታል ውስጥ ወይም የተማሪ መታወቂያ ማግኛ መሳሪያ በመጎብኘት እና የልጅዎን መረጃዎን - የተማሪ ስም ፣ የትውልድ ቀን ፣ ክፍል ፣ ዋና ዚፕ ኮድ በማስገባት ለማግኘት ይችላሉ።
    - የተማሪ ልዩ የምዝገባ ኮድ - ለዚህ የፈተና የጊዜ መስኮት በልጅዎ ትምህርት ቤት ለእርስዎ የሚሰጥ
- ለመግባት በቤተሰብ ፖርታል ውስጥ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ይከተሉ

## በሪፖርቱ ውስጥ ምን ያገኛሉ

በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች የዘንድሮው የውጤት ሪፖርቶች። እነዚህ ሪፖርቶች አብሮ የተቀናበረ የውጤት ሪፖርት ማሳያን ያካትታሉ። የውጤት ሪፖርት ዋና ክፍሎችን የሚያብራራ መሳሪያንም ያካትታል። ሪፖርቶችን እና ማብራሪያዎችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ዝርዝር መመሪያዎችን ከKite የቤተሰብ ፖርታል የተጠቃሚዎች መመሪያ ውስጥ ያገኛሉ።